# ፖለቲካ ከፕሮፖጋንዳ የማይለዩ … (፪)

**ዮናስ 07/03/14**

መነሻችን ምርጫ 2007 እና ይህንኑ ምርጫ ታሳቢ አድርገው የቅድመ የውህደት ስምምነት ያደረጉ ሁለት ፓርቲዎችን (መኢአድና አንድነት) አድርገን ከኢትዮ ምህዳር ቅፅ 02 ቁጥር 73 የአቶ ታዲዮስ ታንቱን መነፅርና የመኢአድን ሰሞንኛ ገመናዎች ተውሰን ፓርቲዎቹ ፖለቲካን ከፕሮፖጋንዳ አለመለየታቸውን በክፍል አንድ ላይ አንስተናል፡፡ በክፍል አንድ ያየነውና ከዚህችው ጋዜጣ ላይ ሁለት መነፅሮች ተውሰን ፓርቲዎቹን እንድንፈትሽ ባሰርነው የብዕር ውል መሰረት እንዲህ በአዲስ መስመር ከአቶ አሰግድ ገ/ስላሴ ተቃዋሚዎችን የተመለከተ እይታ እንቀጥላለን፡፡

‹‹ውስጣዊ ጥራት ለተቃዋሚ ፓርቲዎች›› በሚል የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ለመፈተሽና የፍተሻውም ውጤት ፖለቲካን ከፕሮፖጋንዳ ስላለመለየታቸው በማሳየት የሚደመድመው የአቶ አሰግድ ወቀሳ ከፊሉ ልክ እንደ አቶ ታዴዎስና የተቃዋሚዎቹ መግለጫ ገዢው ፓርቲ ላይ ያጠነጠነ መሆኑ በአጠቃላይ የዓውዱን ፖለቲካ ከፕሮፖጋንዳ አለመየትና የእውር ድንብር ጉዞ የሚያመላክት ነው፡፡

የፅሁፋቸው ጭብጥ ከላይ የተመለከተው ነው፡፡ እናም ከላይ በተመለከተው ርዕስ የተቀነባበረው ፅሁፋቸው በቀጥታ ገዢው ስርዓት ላይ ላለማረፍና ለማስመሰል ከ1960ዎቹ ወይም ከዘውዳዊው ስርዐት ይነሳል፡፡ መነሳቱ ባይከፋም ከፅሁፋቸው ጭብጥ ወይም ከዋና ትኩረታቸው ጋር በምንም መልኩ የማይገናኙ ሃሳቦችን ያነሱና ከኢህአዴግ ነጥለው ህወሃት ላይ ያርፋሉ፡፡ ከዚያም እንዲህ ሲሉ ወደተቃዋሚዎቹ ዋነኛ አጀንዳ እንዲህ ሲሉ ዘለቁ፡፡ ‹‹አሁን በሃገራችን ያለው ‹‹አውራ ፓርቲ›› ነኝ እያለ የሚኩፈስብን የህወሃት ቡድንም ከጥንቱ ከጠዋቱ ጀምሮ ‹‹ ውስጠ - ዴሞክራሲ ይኑር፣ ቡድናዊነት አካባቢያዊነት (አውራጃዊነት)፣ የዘመድ አዝማድ አሰራር ይወገድ፣ ለሃገር ሉዓላዊነት እንታገል፣ ጠባብነት ይወገድ፣ የመገንጠል ጥያቄ ከየት የመጣ ነው? የኤርትራ የመገንጠል ጥያቄ የህወሃት መሪዎች ብቻ የሚመልሱት ሳይሆን፣ በኢትዮጵያ ህዝብ ምርጫ በሚቋቋመው መንግስት

አማካኝነት ነው፣ ፀረ - ደርግ የሆኑ ፓርቲዎችን መምታቱ ይቁም፣ አመራራችን በዴሞክራሲያዊ መንገድ በጉባኤ ይመረጥ፣ ልዩነታችንን በሂደት እያጠበብን ከሁሉም የአንድነት ሃይሎች እና ፀረ ደርግ ኃይሎች ጋር እንተባበር›› ያሉ ብዙ ወገኖች ተሰደዋል፣ ደብዛቸው ጠፍቷል፡፡

‹‹... እስከአሁንም›› ካለ እኔ አውራ ፓርቲ የለም›› በማለት በውስጡም በሃገራችን በነበሩ እና ባሉ ፓርቲዎች ስጋት በመፍጠር በነፍጥም እየጠራረገ በውስጣዊም የሚቃወሙት አባላቱን እያባረረ፣ የሃገራችን አንጡራ ሀብት አሟጦ ለዘር ማንዘሩ በማሸከም ሥርዓቱ ውስጡ በስብሶ፣ ከመዋቅሩ ተነጥሎ በጥቂት ባለስልጣናት ብቻ በአየር ላይ ተንጠልጥሎ ይገኛል፡፡ መጨረሻውም እንደመንግስቱ መጥፎ አወዳደቅ ያጋጥመዋል፡፡›› ከብዙ በጥቂቱ ወደሃገራችን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ፍተሻቸው ለማምራት አቶ አሰግድ አንዴ ህወሃት ላይ ቀጥሎም ስርዓቱ ላይ በጥቅል ከወረወሯቸውና ለፅሁፋችን ጭብጥ ሁነኛ ማሳያዎች ከላይ የተመለከቱትና በተለይም የተሰመሩባቸው ነጥቦች (መስመር የኔ) ወሳኝና መጀመሪያ መታየት ያለባቸው መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ የብሄሮች አድልዎና ጭቆና በህዘቦች ላይ የሚደርስ ጭቆና በመሆኑ የሚፈታውም ግለሰቦችን በሚመለከት የጥገና መፍትሄ ሳይሆን ህዝቦችን እንደ ህዝብ በሚመለከት መፍትሔ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከዚያ አኳያ ስር ነቀል ፖለቲካዊ መፍትሔ ማስቀመጥ የማይታለፍ ጉዳይ የነበር መሆኑን አቶ አሰገደም ያውቁታል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ መሰራት የነበረበት ስራ ግለሰቦችን ወይም ቡድኖችን ሳይሆን ህዝቡን የስልጣን ባለቤት ማድረግ ነው፡፡ የስልጣን ባለቤትነትን ለሁሉም ብሄረሰቦች በእኩልነት ማረጋገጥ አስፈላጊ እንደነበርም ይታወቃል፡፡ ይህንን ለማድረግ እያንዳንዱ ብሄረሰብ የራሱና የአካባቢውን ጉዳይ ማንም ሌላ አካል ጣልቃ ሳይገባበት መወሰን የሚችልበት የተሟላ ስልጣን እንዲሰጠው መደረግ ነበረበት፡፡ ይህንን ለማድረግ ብሄር/ብሄረሰቦች ራሳቸውን በክልል ደረጃ ለማደረጃት ያልቻሉትም ቢሆኑ በልዩ ዞንና በልዩ ወረዳ ወዘተ እንዲያደራጁ ፣ በዚህ መልኩ ከተደራጁ በኋላ ብሄረሰቦች በጋራ ጉዳዮች ለይተው የቀረውን ስልጣን ሁሉ ለክልሎች የሚሰጥ ፌደራላዊ ስርአት የተመሰረተ መሆኑም እሙን ነው፡፡ ክልሎች በህገ-መንግስት ተለይቶ በተሰጣቸው ስልጣን ክልል ማንም የበላይ ሳይደርስባቸው፣ ሌላው ቀርቶ ፌደራልና የክልል መንግስታት አንዱ የበታች ሌላው የበላይ ስርዓት ሳይሆን ሁለቱም በየስልጣን ክልላቸው ሉዓላዊ የሆኑ መንግስታት እንዲሆኑ

መደረጉንም አቶ አሰገደ ከማወቅም አልፈው ተሳትፈውበታል፡፡ ይህ ፌደራላዊ የስልጣን ክፍፍል በህገ-መንግስቱ ምእራፍ 5 አንቀፅ 2 ሰፍሮ ይገኛል፡፡

ብሄር ብሄረሰቦች የራሳቸውን ጉዳይ በራሳቸውና የጋራ ጉዳይን በእኩልነት የሚወስኑበት ፖለቲካዊ ሁኔታን መፍጠር የብሄራዊ ጭቆናና አድልዎን ፖለቲካ መሰረት ለመናድ ወሳኝ እርምጃ ቢሆንም ይህ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ የብሄሮችን መብትና እኩልነት ለማረጋገጥ በተጨማሪ ፖለቲካዊ እርምጃ መወሰድ እንደነበረበት አቶ አሰገደም አብረው ያጸደቁት ጉዳይ ነው፡፡ ብሄር ብሄረሰቦች የራሳቸውን እድል በራሳቸው የመወሰን እስከመገንጠል ድረስ ያለውን መብታቸውን ማረጋገጥም እጅግ አስፈላጊ እንደነበር ዛሬ ከየት መጣ ብለው ቢናገሩም በወቅቱ እርሳቸውም የወሰኑበት ጉዳይ ነው፡፡ እርሳቸው አምነውበት ባይሆን እንኳዋን ይህንኑ መብት በኢትዮጵያ ማረጋገጥ እጅግ አስፈላጊ የሆነባቸው ሶስት መሰረታዊ ምክንያቶች ነበሩ፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ በብሄራዊ ጭቆናና አድልዎ የተማረሩት ህዝቦች የእኩልነት መብታችው ላይ በተጠቀሰው አኳኋን ይከበርላችኋል ስለተባሉ ብቻ ተማምነው የህዝባዊ አንድነትን አማራጭ ይከተላሉ ማለት አይደለም፡፡ ‹‹ምናልባት ሁኔታዎች ተለዋውጠው የተባለው የእኩልነት መብት የተገፈፈስ እንደሆነ ምን ዋስትና አለን?›› ማለታቸው አይቀርም፡፡ በተጨባጭም ከታጠቁት የብሄር/ብሄረሰቦች ድርጅቶችና በአንዳንድ አካባቢ ከህዝቡም ጥያቄው በሽግግሩ ዘመን ማብቂያ ላይ ጎልቶ መነሳቱን እነአቶ አሰገደ ያስታውሳሉ፡፡ ህገ-መንግስቱ የመገንጠል መብት እንደሚያስከብር ሲያረጋግጥ እኩልነት ይመቸናል፣ በሆነ ምክንያት እኩልነቱ የተሰናከለ እንደሆነ ደግሞ ከአንድነቱ መውጣት እንችላለን ስለሆነም ተማምነን መቀጠል እንችላለን ያሉበት ሁኔታ መፈጠሩንም እንዲሁ፡፡ እናም ጭቁን ብሄረሰቦች መብታቸው እንዳይረገጥ የመጨረሻ ዋስትና የሚሆናቸው በመሆኑ ተማምነው የእኩልነትና የዴሞክራሲያዊ አንድነትን አማራጭ እንዲከተሉ ለማድረግና የህዝቦችን አንድነት ለማጎልበት መብቱ እስከመገንጠል ድረስ የሚዘልቅ መሆኑ እጅግ ተፈላጊ የሆነና ምንጩም የታወቀ ነው፡፡

የዚህ መብት መረጋገጥ ተፈላጊ የሚሆነው ጭቁን ብሄሮች/ብሄረሰቦች በሂደት ብሄራዊ ጭቆና እንዳያገረሽ ዋስትና እንዲሆናቸው ብቻም አይደለም፡፡ ብሄራዊ ጭቆና መልሶ እንዲያቆጠቁጥ ለማድረግ የሚያስብ ሃይል ካለ በዚሁ አላማ እንዳይገፋበት ለመግታት እንጂ፡፡ ብሄራዊ ጭቆናና አድልዎን በህዝቦች ላይ ለመጫን የሚፈልግ ሃይል ይህ መብት

ካለ አላማው እንደማይሳካለት ግልፅ ሊሆንለት ይችላል፡፡ ምክንያቱም ጭቁን ብሄር ብሄረሰቦችን መልሼ ልጫናችሁ ቢል ዘወር በል ብለው የየራሳቸውን ነፃ መንግስት ማቋቋም እንደሚችሉ ይገነዘባል፡፡ ስለሆነም ብሄራዊ ጭቆናን ለመመለስ የሚፈልግ ሀይል ከዚሁ አላማ እንዲታቀብ በማድረግ የመብቱ መከበር የህዝቦች እኩልነትና አንድነት ዋስትና እንዲያገኝ የሚያደርግ እንጂ ከፋፍሎ ለመግዛት ጂኒ ቁልቋል አይደለም፡፡

እጨቆናለሁ ብሎ ለሚሰጋው ዋስትና ሰጥቶ በማረጋጋጥ እጨቁናለሁ ብሎ የሚያስበውም ተጨቋኙን ለቆ ባዶ እጁን እንደሚቀር ተገንዝቦ ከዚሁ አላማ እንዲታቀብ በማድረግ የዚህ መብት መረጋገጥ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ህዝባዊ አንድነትን ለማረጋገጥ ፍቱን መድኃኒት ሆኖ ያገለግላል፤በማገልገል ላይ መሆኑንም አረጋግጠናል፡፡ ስለሆነም መብቱ ተፈላጊ የሚሆነው በወሳኝነት የብሄራዊ ጭቆናን ፖለቲካዊ መሰረት በመናድ በመፈቃቀድ ላይ ለተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ  አንድነት የተመቻቸ ሁኔታን በመፍጠሩ ነው፡፡

የመገንጠል መብት ተፈገላጊ የሚሆንበት ሌላም ምክንያት አለ፡፡ አንድ ህዝብ በማንኛውም ምክንያት ኢትዮጵያዊ ሆኜ አልቀጥልም ካለ በሰላም ሊሰናበት የሚችልበትን እድል ለማመቻቸትም ጭምር ነው፡፡ ይህ ተፈላጊ የሚሆነው ከመርህ አኳያ ሲታይ ኢትዮጵያዊነት ዜጎች ወደውና አምነውበት የሚቀበሉት ክብር እንጂ ሳይወዱና ሳያምኑበት ተገደው የሚጫንባቸው ዕዳ መሆን ስለሌበት ነው፡፡ ይህ ተፈላጊ የሚሆንበት ሌላው ምክንያት አንድን ህዝብ በሃይል ላኑር ላሳድር ቢባል እንኳን ውጤቱ ተላልቆ በእንደዚህ አይነቱ ሁኔታ የተሻለው አማራጭ የመገንጠል መብትን እውን በማድረግ በሰላም መለያየት ነው፡፡ በርግጥ የመገንጠል መብት በህገመንግስቱ መሰረት ተግባራዊ በሚሆንበት ወቅት ሁከትና ግጭት በፍፁም ሊከሰት አይችልም ማለት አይደለም፡፡ በአገራችን ያለው የህብረተሰብ ጥንቅርና የተወሳሰበ የህዝቦች አሰላለፍ ግምት ውስጥ ሲገባ መብቱ ተግባራዊ ሲሆን ሰላም የመናጋቱ አደጋ የጎላ እንደሆነ የሚካድ አይደለም፡፡ በመሆኑም የመገንጠል መብት እንዲሁ በቀላሉ ተግባራዊ ለማድረግ የሚሞከር ጉዳይ ሊሆን አይገባም፡፡ ይሁንና የህዝቡ ጥያቄ ገፍቶ ከመጣ ከሰላምም አኳያ የተሻለ አድል የሚኖረው በሃል ለማቆየት በመሞከር ሳይሆን በሰላም በህገ-መንግስቱ መሰረት በመለያየት ነው፡፡

አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከላይ የተጠቀሱትን ሶስት እርምጃዎች በመውሰድ፣ የብሄራዊ ጭቆናና አድልዎን ተቋማዊ መዋቅራዊና ፖለቲካዊ መሰረት በመናድ አገራችንን ከእልቂትና ከመበታተን ለመታደግ የሚያስችል ታሪካዊ ተግባር ፈፅሟል፡፡ ብዙዎች

እንደገመቱትና አንዳንዶቹ እንደተመኙት እርስ በእርሳችን ሳንፋጅና ሳንበታተን በእኩልነትና ዴሞክራሲ ጎዳና ለ23 አመታት መጓዝ ችለናል፡፡ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚቃወመው  አቶ አሰገደ እና መሰሎቻቸው እንደሚሉት ኢትዮጵያዊነትን በአጠቃላይ ሳይሆን በፀረ-ዴሞክራሲ ላይ የተመሰረተውንና ለፀረ-ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ፣ ለብሄራዊ ጭቆናና አድልዎ ርእዮተ አለማዊ መሰረት ሆኖ የነበረውን ኢትዮጵያዊነት ብቻ ነው፡፡

ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ኢትዮጵያዊነት ማንም ህዝብ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ እስከተፈጠረ ድረስ ወደደም ጠላም ኢትዮጵያዊ ሆኖ መቀጠል አለበት ይላል፡፡ አዲሱ የኢትዮጵያዊነት አስተሳሰብ ኢትዮጵያዊነት የሚመኙት ክብር እንጂ የሚጋቱት መዘዝ አይደለም፡፡ ስለሆነም ኢትዮጵያዊ የሚሆነው ኢትዮጵያዊ ነኝ ብሎ ያመነና በዚሁ የሚኮራ ብቻ መሆን አለበት ይላል፡፡ ይህንኑ ያልፈለገ ማንም ሰው ወይም ህዝብ በምንም መልኩ ኢትዮጵያዊነትን ሳይወድ እንዲቀበል መደረግ የለበትም ይላል፡፡ ስለሆነም ፀረ-ዴሞክራሲው ኢትዮጵያዊነት ለግዛት አንድነት በመሟገት የመገንጠልን መብት አምርሮ ሲቃወም ዴሞክራሲያዊ ኢትዮጵያዊነት ለህዝቦች አንድነት ብቻ በመቆርቆር ለመገንጠል መብት በፅናት ይቆማል፡፡

ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ኢትዮጵያዊነት(የወቅቱ ተቃዋሚዎች) ሁሉም ህዝቦች ለአገራቸው እኩል ይቆረቆራሉ ብሎ አያስብም፡፡ ስለሆነም አንደኛውን ህዝብ ታማኝ ሌላውን ተጠርጣሪ ያደርጋል፡፡ ተጠርጣሪው በዋነኛነት የጭቁን ብሄር/ብሄረሰቦች ህዝብ ስለሚሆን ያ ህዝብ የራሱን ቋንቋ እንዲጠቀም፣ ባህሉን እንዲጠብቅና እንዲንከባከብ፣ ታሪኩን እንዲያውቅ አይፈልግም፡፡ ይህን ካደረገ የኢትዮጵያዊነት መንፈስ እንደጎደለው ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ የአንድ ብሄር  ቋንቋ፣ ባህል፣ ታሪክ ወዘተ በግድም ቢሆን የሁሉም እንዲሆን ይፈልጋል፡፡ ወጥ የሆነ ህዝብ፣ የተቀየጠ ህዝብ ካልሆነ አያምርም በሚል መፈክር ብሄራዊ ማንነትን በማጥፋት ፖሊሲ (Assimilation) ህገ ወጥ የሆነ የተቀየጠ ህዝብ እንዲፈጠር ይፈልጋል፡፡ በእኩልነት፣ ልዩነቶችን በማቻቻል የሚያምን የዴሞክራሲ መንገድን ተፃሮ ልዩነት የሌለበት የእኩልነት ደብዛ የጠፋበት የፀረ-ዴሞክራሲ አለምን ይመኛል፡፡

ዴሞክራሲያዊ ኢትዮጵያዊነት ሁሉም ህዝቦች ኢትዮጵያውያን የሚሆኑት ተገደው ሳይሆን አምነውበት ኮርተውበት ነው ብሎ ያምናል፡፡ ተገዶ በፀረ-ዴሞክራሲያዊ አኳኋን ኢትዮጵያዊ መሆን በፍፁም መታሰብ የሌለበት ነው ይላል፡፡ ሁሉም ህዝቦች በነፃ ፍቃዳቸው አንድ የመግባቢያ ቋንቋ የመረጡ ቢሆንም የኢትዮጵያ ቋንቋ ማለት በአገሪቱ

የሚነገሩ ቋንቋዎች ሁሉ ማለት ነው ብሎ ያምናል፡፡ የኢትዮጵያ ታሪክና ባህልም በተመሳሳይ መልኩ የሁሉም ህዝቦቻችን የቆየ ታሪክና ባህል ድምር ውጤት ነው ይላል፡፡ የምናምረው ብሄራዊ ማንነታችንን አክብረን በህብረ ቀለም አሸብርቀን በመንፈስ ኩሩ ኢትዮጵያዊ ስንሆን ነው ይላል፡፡ አቶ አሰገደም ሆኑ መላው የጠፋቸው ተቃዋሚዎች ያልሰሩትን ፖለቲካ ለማካካስ ከሚጠቀሙዋቸው ፕሮፖጋንዳዎች መካከል የኤርትራ ጉዳይም ይገኝበታል፡፡

የኤርትራ ጉዳይ ሻእቢያ በደርግ ውድቀት ዋዜማ መላውን ኤርትራ የተቆጣጠረበት ሁኔታ ስለተፈጠረ ተወደደም ተጠላም በዚያው ያከተመ ጉዳይ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ በወቅቱ አገሪቱ በቋፍ ላይ በነበረችበት ወቅት እውነታውን አንቀበልም ቢባል እንኳ አዲስ ጦርነት ከፍቶ ወደለየለት መበታተን እንድታመራ ማድረግ ማለት ነበር፡፡ አዲሲቷ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያውያን በመሆናቸው የሚኮሩ ዜጎች እንጂ ኢትዮጵያዊነት ሳይፈልጉ የሚጫንባቸውን ዜጎች ይዛ በሰላምና በዴሞክራሲ ጎዳና በፍፁም መቀጠል እንደማትችል ስለታመነበት እንጂ፡፡ በመሆኑም የኤርትራ ህዝብ ማንነቱን በራሱ ነፃ ውሳኔ ያረጋግጥ የሚለው መርህ ታምኖበት በኤርትራ ረፈረንደም ተካሂዶ ህዝቡ ከሞላ ጎደል በሙሉ ድምፅ የራሱ ነፃ መንስግት ማቋቋም ስለመረጠ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ይህንን የህዝቡን ውሳኔ በፀጋ ተቀብሎ ኤርትራ ነፃ መንግስት ካቋቋመች በኋላ በቁርሾ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን በወንድማማችነት መንፈስ የመልካም ጉርብትና ግንኙነት ለመመስረት ተሞክሮ ቢያንስ ለሰባት አመታት ይኸው ተሳክቶ በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል ሰላም ሰፍኖ እንደነበር የታወሳል፡፡ የተገኘው ፋታ ሌሎችንም ጥያቄዎች በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ ለመፍታት በር መክፈቱም እንዲሁ፡፡

በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነት እንደሚጠቅመው እያንዳንዱ ህዝብ ከተቀበለ ቀጥሎ የሚመጣው ጉዳይ ይህንን አማራጭ ማን ያረጋግጥልኛል የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ በአንድነት መኖር የፈለገ ህዝብ ብቻውን የዴሞክራሲያዊ አንድነት ዋስትና ሊሆን አይችልም፡፡ ይህንን ማድረግ የሚችሉት የሁሉም ብሄሮች አርሶ አደሮች ላብ አደሮች በአጠቃላይ የዴሞክራሲ ሃይሎች በትክክለኛ የዴሞክራሲ መስመር ላይ የተሰባሰቡ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ አብዮታዊ ዴሞክራሲ እንደዚህ አይነቱን የሃይል ስብስብ ፈጥሮ ነው የቀረበው፡፡ አንዱ የሌላውን መብት አክብሮ በአጋርነት የሚሰለፍበት እንጅ እንደ አንዳንድ ተቃዋሚዎች

የጥቂቶች የበላይነት የገነገነበት ሳይሆን አንዱ በሌላው ላይ ሳይጫን ለጋራ ጥቅምና አላማ የሚሰባሰቡበት መድረክ ነው የተፈጠረው፡፡ ።

ኢህአዴግ የሁሉም ብሄሮች የዴሞክራሲ ሃይሎችን በዴሞክራሲያዊ አላማ ዙሪያ በማሰባሰብ አንዱ የሌላው አጋርና ዋስትና በመሆን አንዱ በሌላው ላይ ተማምኖ በጋራ በእኩልነት ሊራመዱ የሚችሉበት ሁኔታን በመፍጠር ሰላምና የዴሞክራሲ ጎዳና ዋስትና እንዲገኝ ፣የመበታተን የእልቂት መንገድ እንዲቀረፍና እንዲወገድ ያደረገ እንጂ መላው የጠፉቸው ተቃዋሚዎች ምርጫ 2007ን ታሳቢ አድርገው እንደሚሉት ለመጠፋፋት የሚሰራ አይደለም፡፡ የጥፋት መንገዱ እውን ሳይሆን የቀረው ትክክለኛ መስመር በመቀየሱ ብቻ ሳይሆን የሰላምና የዴሞክራሲ ሃይሎች በአንድ የጋራ ግንባር ለመሰባሰብ በመቻላቸው ጭምር መሆኑም ሊሰመርበት ይገባል፡፡

ዴሞክራሲ ከአምባገነን ስርዓቶች የተሻለና የላቀ የሚሆንበት አንዱ ምክንያት ራሱን በራሱ ማረም የሚችል ስርዓት መሆኑ ነው፡፡ ዴሞክራሲ ራሱን በራሱ ማረም የሚችለው ህዝቡ የመናገር ፣የመጻፍ ወዘተ መብቱን ተጠቅሞ በስልጣን ላይ ያለውን ፓርቲ ሂስ ሊያደርግ ስለሚችልና በስልጣን ላያ ያለውን ፓርቲም ይህንኑ አድምጦ መስተካከል የሚገባውን ነገር ሊያስተካክል ስለሚችል ነው፡፡ በዚሁ መልኩ መስተካከል ካልቻለም ህዝቡ የመምረጥ መብቱን ተጠቅሞ በስልጣን ላይ ያለውን ፓርቲ ሽሮ ሌላ ፓርቲ ስለሚሾም ነው፡፡ ይህ አሰራር ፓርቲዎች ለራሳቸው ብለው እንዲጣፍጡ ካልጣፈጡም በምርጫ ‹ድንጋይ ነህ!› ተብለው እንዲጣሉ በማድረግ ግድፈቶች ሁኔታው በሚፈቅደው መጠን እንዲወገዱ ስለሚያደርግ ተመራጭ አሰራር ይሆናል፡፡

አብዮታዊ ዴሞክራሲ የገነባው ዴሞክራሲ ገና ታዳጊ ዴሞክራሲ በመሆኑ በርካታ ጉድለቶች እንዳሉት የማያጠያይቅ ነው፡ በህዝቡ ውስጥ ያሉ የጥገኝነት አስተሳሰቦች ግንባሩ ከህዝብ የተፈጠረ ነውና በግንባሩም ውስጥ መታየታቸው በፍጹም የማይቀር ነው፡፡ ስለሆነም ዴሞክራሲያችን ከስህተቶች የፀዳ እንዳልሆነና የፀዳ ሊሆንም እንደማይችል ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ እንኳንና የኛ በኋላ ቀር አገር እየተመሰረተ ያለ ታዳጊ ዴሞክራሲ በበለፀጉት አገሮች የሚሰራበት ዴሞክራሲም ቢሆን እንከን የለሽ አይደለም፣ እንከን የለሽ ሊሆንም አይችልም፡፡ ስለሆነም ዴሞክራሲያችን በተቻለ መጠን ስህተቶቹ መፈጸማቸው ስለማይቀር ሲፈጸሙ ፈጠን ብሎ ማስተካከል ይገባዋል፡፡ ራሱን በራሱ ማረም የሚችል ስርዓት መሆን ይገባዋል፡፡ እየተገነባ ያለው ዴሞክራሲ እንደዚህ አይነት

ባህሪ ያለው መሆኑ በግልፅ እየታ እና እየታወቀ እነ አቶ አሰገደ እና መሰሎቻቸው በውስጠ ዴሞክራሲ ችግር የተጠቃ ስርአት አድርው ፕሮፖጋንዳቸውን ይነዛሉ፡፡

በመጀመሪ ደረጃ ግንባሩ ስህተቶችን ለመቀነስ፣ ከተፈጠሩም በኋላ ሁሉም በሚማርበት አኳኋን ለማስተካከል በሂደት እያዳበረው የመጣ የግምገማና የግለ-ሂስ ባህል አለው፡፡ይህ ድርጅቱ ዴሞክራሲያዊ ባህል በተቻለ መጠን ስህተቶችን ለመቀነስ ከዚያም አልፎ ከስህተቶቹ በቂ ትምህርት ወስዶ እንዲያስተካክል የሚረዳው ስርዓቱ ራሱን በራሱ የሚያስተካክልበት አንድ መሰረታዊ መንገድ ነው፡፡ ድርጅቱ በውስጡ ከሚያደረገው ግመገማ ውጪ በየወቀቱ የተለያዩ የህዝብ መድርኮችን እያዘገጀ በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ህዝቡን የሚያወያይና እያወያየ መሆኑም ይታወቃል፡፡ በነዚህ መድረኮች ከሚነሱት ጥያቄዎችና አስተያየቶች እየተነሳ ራሱን በራሱ እንደገና ይፈትሻል፣ እየፈተሸ በመሆኑም የተገኙት ውጤቶች ምሽክሮች ናቸው፡፡ ይህ ስርዓቱ ራሱን በራሱ የሚያስተካክልበት ሌላው መሳሪያው ነው፡፡

ከትጥቅ ትግሉ ወዲህ በእንደዚህ ዓይነቶቹ የውስጠ ድርጅት መድረክና ከህዝቡ ጋር በሚከናወኑ መድረኮች አማካኝነት ራሱን ደግሞ ደጋግሞ ያልተፈተሸበት ዓመት እንደሌለ ከአቶ አሰገደ በላይ ማን ይናገር የነበረ ማለት ነው፡፡ በእነዚህ መድረኮች አማካኝነት መለስተኛም ሆነ ስር-ነቀል ማስተካከያዎች ወሰዷል፡፡ በስር ነቀልነቱ በምሳሌነቱ ሊጠቀስ የሚችለው የድርጅቱ የተሃድሶ እንቅስቃሴ ነው፡፡ የተሃድሶ እንቅስቃሴው በድርጅቱ ውስጥ በአንድ በኩል ስልጣንን የኢኮኖሚያዊ ሃብትና የብልጽግና መሳሪያ በማድረግ የተለመደውን ፀረ ዴሞክራሲያዊና የነፃ ገበያ ስርዓት በአዲስ መልክ ለመገንባት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ስልጣን የሃብት ምንጭ እንዳይሆንና በአገራችን የሚገነባው ስርዓት በሁሉም መልኩ ዴሞክራሲያዊ የነጻ ገበያ ስርዓት እንዲሆን በተለይም ደግሞ ዴሞክራሲና ዴሞክራሲያዊ አንድነት እንዲዳብር ፣ማናቸውም የጥገኝነት አስተሳሰብ በህበረተሰባችን ውስጥ የበላይነት አግኝቶ የጭቆና ስርዓት እንደገና እንዳይመለስ በሚፈልጉ ሃይሎች መካከል የተካሄደ ትግል ነው፡፡

በኢህአዴግ ውስጥ በአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ በጥገኝነት መካከል የተካሄደው ውስጠ-ደርጅት ትግል ሂደት በድርጅቱ መስመሮችና አሰራሮች ዙሪያ እጅግ መሰረታዊ የሆኑ ለውጦችን ያስከተለ በድርጅቱ ውስጥ ሰፋ ያለ ሰው ሃይል ሽግሽግን የጠየቀ ነበር፡፡ ጎላ ብሎ የሚታየው የተሀድሶው እንቅስቃሴ ቢሆንም በየጊዜው ከፍተኛ ትርጉም ያላቸው

ግምገማዎች እየተደረገ ኢ.ህአዴግን ሰህተቶቹን እንዲያርምና ከነሱም እንዲማር ለማድረግ ረድተውታል፡፡ ድርጅቱ በውስጡና ከህዝቡ ጋር በመሆን የህዝቡን ስሜት በማዳመጥ የሚያደርጋቸውን ራስን በራስ የማረም ጥረቶች እጅግ መሰረታዊና ፋይዳ ያላቸው ቢሆኑም የመጨረሻ ዋስትና ሊሆኑ አይችሉም፡፡ የመጨረሻው ዋስትና ተግባራዊ የሆነው ዴሞክራሲ ነው፡፡

ህዝቡ የዴሞክራሲ መብቱን በመጠቀም በፅሁፍ በንግግር ከሚያደርገው ማስተካከያ አልፎ በምርጫ ካርዱም የማስተካከያ እርምጃ የሚወሰድበት እድሉ አለው ብቻ ሳይሆን በሶስተኛው አገራዊና ክልላዊ ምርጫ እንደታየው በተግባርም ይጠቀምበታል፡፡ ህዝቡ ብሶታችንን ኢ.ህአዴግ አላዳመጠንም በማለትና በጥገኞች ከንቱ ተስፋ ተደናግሮ በብዙ አካባቢዎች ኢ.ህአዴግን ሳይመርጥ ቀርቷል፡፡ ጥገኞች አገሪቱን ቢቆጣጣሩ ኑሮ በዴሞክራሲያችንና በህዝቡ ወደፊት እድል ላይ ሊከተል ይችል የነበረውን አደጋ ለመገመት የሚያዳግት ቢሆንም ህዝቡ ካርዱን እንደመጨረሻ መሳሪያ ሊጠቀምብት እንደሚችል አውቆና አምኖ ይህንኑ መሳሪያ መጠቀሙ ስርዓቱ ራሱን በራሱ ማረም የሚችል መሆኑን በተጨባጭ ያረጋገጠ ተግባር ነው ፡፡